# <u>አዴኃን በመተማ ከተማ ጥቃት ሰነዘረ</u>

01252018

በሰሜን ጎንደር የወያኔ ደህንነቶች መከማቻ ሆና በምትገኘው በመተማ ከተማ አዲስ ዘመን ሆቴል የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ(አዴኃን) ትላንትና ማለትም ጥር 15÷2010 ዓ.ም ከምሽት 2:30 ላይ የህወሃት ወያኔ ቀኝ እጅና የሆቴሉ ባለቤት በሆነው ሀዲሽ በላዕይ እና አብረሁት የሚሰሩ ሰላዮች ስብስብ ላይ በእጅ ቦንብ ጥቃት ፈፅሟል፡፡በተደረገውም ጥቃት ይህ መረጃ እንቀሚወጣበት ጊዜ ድረስ 3 በአደገኛ ጉዳት ላይ ሆስፒታል የሚገኙትን ጨምሮ 8ቱ ላይ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡ግዳጁን የፈፀሙት የአዴኃን መቺ ታጋዮች በሚፈለገው ቦታ በሰላም እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡አዴኃን የአማራ ህዝብን ሲያፍኑ፣ሲያስገድሉ እና ሲያሳድዱ የቆዩ የህወሃት ሰላዮች ላይ በየትኛው ቦታ እና ጊዜ እርምጃውን እንደሚቀጥል አጥብቆ ይገልፃል፡፡

ትግላችን የአማራ ህዝብ እየደረሰበት ካለው ልዩ የሆነ የፖለቲካ፤የኢኮኖሚ፤የማህበራዊ፤የስነ-ልቦናና የዘር ጥቃት ነፃ ወጥቶ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባትና ለዚህም የሚቆሙ ነፃና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማት ዕውን የሚሆኑባት፤የኢትዮጵያ ህዝብ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባት፤የህዝብ አንድነት፤ፍቅርና እኩልነት የጠነከረባት፤ጠንካራና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ሆና ማየት።ለዚህም የማንከፍለው መስዋዕትነት አይኖርም፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

የአለቅነው አልቀን ወያኔ ይደመሰሳል፤አማራው ከታወጀበት የዘር ማጥፋትና ማፅዳት እራሱን ይታደጋል!!!